# ጨረቃና ፀሐይ

## (አጫጭር ግጥሞች)

ከጌታሁን ያ አብርሃም

2000(2007)

ISBN 978-91-633-0969-4

© 2007 ደራሲው/Författaren

ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| ውሃ | 1 |
| በአውቶብስ ላይ | 2 |
| መጠርጠር አይሻም | 4 |
| እምቢታ | 5 |
| በሀሳብ ፈረስ | 6 |
| አብዶ ይሆን? | 8 |
| አለምኩ | 9 |
| የአገር ሽማግሌ | 10 |
| መላው ቢጠፋበት | 11 |
| ግንቦት ጠባላቸው | 12 |
| እቃዣለሁ | 13 |
| ትላንት ዛሬ ነገ | 14 |
| ጢስ እሳት | 15 |
| ባይተዋር | 16 |
| ብቸኝነት | 17 |
| የአገር ቤት አውደ አመት! | 18 |
| ድግስ | 19 |
| ጨረቃና ፀሐይ | 20 |
| አንድ ቀን | 21 |
| እውነትን አፋልጉኝ | 22 |
| መሰላል | 24 |
| ድልድይ | 26 |
| ባሕር ሆደ ሰፊው | 27 |
| ውጥንቅጥ | 28 |
| ትውልዳችን | 30 |
| ጠዋት በማለዳ | 31 |
| የሰላም አጋር ነኝ | 32 |
| አሁን | 34 |
| ለሁለተኛው ሺ ዓመት ምህረት | 35 |

በርካታ ግጥሞቼ በተለያዩ ምክንያቶች በየቦታው ተበታትነው የቀሩ ቢሆንም፣ ዛሬ በእጄ ካሉት ጥቂቶቹን አሰባስቤ አቅርቤያለሁ። መታሰቢያነትዋ ለባለቤቴ ለዘመዶቼ ለጓደኞቼ ለወዳጆቼና ለስነ ግጥም አፍቃሪዎች ይሁን።

**ውሃ**!

**ውሃ**! **ውሃ**! **ውሃ**!
**ውሃ**! **ሕይወት**
**ውሃ**! **ቅስፈት**፣
**ውሃ**! **ልማት**
**ውሃ**! **ጥፋት**።

1983

በአውቶብስ ላይ

በር ከፊት ቲኬት ቆረጥ
ልግባ እያለ ያም ይህም
በየፊናው መንፈራገጥ
አ! አ!እጄን! እጄን! እግሬን!
እግሬን! አሁን ዝጋ
የአውቶብስ ላይ ጣጣ ጅምር
ወደ መሃል መጠጋጋት ሽርሽር
ፌርማታ ላይ ጥቂት ወርዶ ጥቂት ጨመር
በሰወ ብዛት መተፋፈን መተፋፈግ
አይ ጎረምሳ በዚህ አሳቦ
ከኮረዲት ፊት ከጀርባ መፈጋፈግ፣
ሌላው ደግሞ ከዚህ ሆኖ ከማዶዋ መጠቃቀስ
ያቅራቢያውን መቆናጠጥ መተናኮስ
አይ አውቶብስ!
ጩልፋቱም በጥበቡ ኬላ ሳይቆም ወይ ቢሮ በር
ያለ ፈቃድ ሲበረብር ሲመዘብር
ደሀ ሀብታሙን ሲመረምር
መአድን ሊያገኝ ሲቆፋፍር
ቢሳካለት ይዞ ሊበር!
ስንቱ ቅጡ
የአውቶብስ ላይ ውጥንቅጡ።
እማማ ከዝች ጋ ቁጭ ይሉ?
እርሶም ልጅ ይዘዋል ከወደዚህ ጋ አረፍ ይሉ?
የትህትናው የአክብሮቱ
የቀልድና ጭውውቱ
መልካም ባህል ማስደሰቱ

ግን ማንጓጠጡ መሳደቡ
ሌላም ሌላም ዲቃላው ባህል ማስጠላቱ፣
አይ አውቶብስ!
አተኩሮ ተመስጦ ከልብ ለሚያይ
ሕይወት አለ ከሕይወት ሕይወት
የሚጨልፉለት
በአውቶብስ ላይ።

1983

## መጠርጠር አያሻም

ሐሰት ብትደነድን ወፍራ እንደ ቱባ
በዘመድ በስልጣን በገንዘብ ብትተባ፣
ልታጠፋት ብትጥር እውነትን አሳዳ
ብታሴርባትም ብዙ እንድትጎዳ፣
ምንም ብትጠወልግ እንደክር ብትቀጥን
ብትሰደድ እንኳን አጥታ መድረሻዋን
ቶሎም ባይሰምርላት ብትጠብቅ ጊዜን
መጠርጠር አያሻም እውነት መሸነፏን።

1990

እምቢታ

የዛሬውን እድገት ብልጽግና አይቶ
ሌሎችን በፍጹም ላይስታውስ ረስቶ
የእኔን ስልጣኔ ማምለክ አለባችሁ
የእኔን ቴክኖሎጅ ማድነቅ አለባችሁ
ሆነና ነገሩ
የጥንት ስልጣኔዎች የጥንቱ እውነታ
ከቶ አይደመጥም ይታያል በእምቢታ
አውሮፓዊ ያልሆነው የኢንካ የአዝያት
የእነ ባቢሎኑ የእነ አክሱማይት
ስራዎች
ቀድመው እንደነበሩ የስልጣኔ እምብርት
የገነቡአቸውን አብያተ መንግስታት
የነጹአቸውንም አብያተ ሃይማኖታት
እጹብ ድንቅ መሆን ፍጹም ታላቅነት
ሊካድ ባይቻልም ሆኖ መራራ እውነት፣
በዚህ በአዲሱ አለም ሲሰጠው እይታ
በብዙዎች በጎሪጥ ይታያል በእምቢታ።
ለብዙዎች ፍጹም የሚሰጠው ደስታ
የተቀረው አለም ከጥንት ጀምሮ
የሚቀምሰው አጥቶ ፍጹም ተቸግሮ፣
በዱር በገደሉ ፍሬ እየለቀመ
እራቁቱን ሁሌም የሚኖር ነበረ
ቢባል
ይህ ነው ለብዙዎች የሚሰጥ እርካታ
ምላሽ የሚሆነው ለክህደተ እምቢታ።
እኛም አሻፈረን እምቢ ነው መልሳችን
እናንተ ስትተኙ እኛ ነቅተናል
ሕንጻዎች አንጸን ግድብ ገድበናል

ከተማ ከትመን ንግድም አስፋፍተናል
ከእናንተ ብዙ እጅ መጥቀን ተጉዘናል።
የእኛ ስልጣኔዎች እስከ አሁን ባይዘልቁም
ለምስክርነት ቅርሱ ግን አልጠፋም።
ታድያ አልሰለጠኑም ልንባል አንችልም
እናንተ ቀዳሚ እኛ ደግሞ ጭራ
ከቶም አይደለንም
ይህ አይነቱን ግምት እምቢ አንቀበልም።

1992

## በሀሳብ ፈረስ

የሀሳቡን ፈረስ-ሽላልሞ ጫነና
ራሱን ሊያስታውስ-የኋሊት ሄደና
ቀድሞ ያለፈበትን-የሕይወት ጎዳና
ክፉውን መልካሙን-አየ በጥሞና።
በዋዛ ፈዛዛ-ያሳለፈው ዘመን
እጅግ ስለበዛ-ተዋጠ በሀዘን
እሱ ሳይሻውም-ያባከነው ጊዜ
ሊመለስ ባይችልም-አየው በትካዜ።
በአንጻሩም ፍሬያማ ሕይወቱ-መልካም የሰራበት
እውቀቱ ጉልበቱ-ለበጎ የዋለበት
ለሰው ስብዕና-ተግቶ የሰራበት
በግልጽ ታየውና-አለው ኩራት ኩራት።
ቀሪውን ዘመኑን-ወቅቱ ቢፈቅድለት
ሊያስወግድ ስንፍናን-በትጋት ለመስራት
ለራሱ ቃል ገብቶ-ምሎ ተገዝቶ
ፈረሱንም ገትቶ-ከሀሳበ ባሕር ወጥቶ
ሄደ ተሰማራ-ወደ እውነታው አለም
በርትቶ ሊሰራ-ሳያቅማማ ፍጹም።

1993

**አብዶ ይሆን?**

**የተተለተለ ቁምጣውን አጥልቆ**
**ወይም**
**ከቂጥ ከጉልበቱ የተቦጫጨቀ**
**ዝልዝል ሱሪ ታጥቆ**
**በየጎዳናው ላይ ሳየው መንሸርሸሩን**
**በማለት ጠየቅኩኝ ይሄ ሰው አብዶ ይሆን?**
**ጸጉሩን ዞርያ ላጭቶ**
**ቁንጮ ከፊት ትቶ**
**ሲንጎራደድ ሳየው ያን ትልቅ ጎሮምሳ**
**ለእኔስ ቢቸግረኝ ስለእርሱ ላወሳ**
**ያው እንደ ልማዴ ሳልረዳ ስቀር ይህን ሁኔታውን**
**በማለት ጠየቅኩኝ ይሄ ሰው አብዶ ይሆን?**

1993

## አለምኩ

በሀሳብ ባህር ጠለቅኩ ብቅ አልኩ
ድርጊቶችን በያይነቱ ተመለከትኩ፣
በእራሴ ፍትህ ሁሉን አየሁ
ይሄ በጎ ያኛው መጥፎ ብዬ አሰላሁ፣
የሚዋጠኝ የሚያዋጣኝ
ይህ ነው አልኩኝ፣
በዝያ ባህር በሀሳብ ጀልባ እየተጓዝኩ
በብዙ አለምኩ በሩቅ አለምኩ አለምኩ አለምኩ…

1994

## የአገር ሽማግሌ

መላ ሲጠፋብህ
    የሚታደግ በምክር
መልካም ስትሰራ
    የሚያበረታታ እንድትጠነክር
ስህተት ስትፈጽም
    በውል የሚቆጣ
ከሰው ስትጣላ
    ዕርቅን የማያመጣ
የአገር ሽማግሌ
    ወዳጅ አያሳጣ።

1995

## መላው ቢጠፋበት

ከዋናው ከተማ ትልቁ ጎዳና
ከስትራጌት ጫፍ ላይ አንድ ጥግ ያዝንና
ከባለቤቴ ጋር የዴንማርክን ጠላ ልንቀምስ ተቀምጠን
የአላፊ አግዳሚውን ትርኢት እናያለን፣
በጋ ስለሆነ ሕዝብ የተራመሳል
ከፊትለፊታችን ከአሮጌው አደባባይ
ብዙ ሰው ተቀምጦአል።
የአገሬው ቦዘኔዎች በቀኝ ከትመዋል
አፍሪካውያኑ በግራ ሰፍረዋል፣
ከአደባባዩም ጠርዝ የተቀመጡ አሉ
አንድም የአገሪ ሰው አለ በመሀሉ።
በቀኝም አይደለም ወይንም በግራ
መጠጥም አይወስድም ከጁ የለ ሲጋራ
እንደ እነሱ አይጨፍር ወይም አያቅራራ
ወይ አይነጋገር ከእነሱ አያወራ
ፈንጠር ብሎ ያያል የሰዎቹን ስራ።
አይቶ አይቶ አይቶ ሲታክት መላው ሲጠፋበት
አልጣመውም መሰል የሰዎቹ ድርጊት፣
ራመድ ራመድ አለ ገባ ከስትራጌት
ከአውራው ጎዳና ውስጥ ሕዝብ ከሞላበት
አይቶ አይቶ አይቶ ሲታክት መላው ሲጠፋበት።

1995

## ግንቦት ጠባላቸው

ግንቦት ጠባላቸው አበቦች አበቡ
ለሙቀቱ ሽምያ ጦፈ ርብርቡ
የክረምቱ ካፖርት ገባ ከመጋዘን
ስስ ሸሚዝ ደርበው ታጥቀው ቁምጣቸውን
ሞልተውት ይታያል ሰዎች ጎዳናውን፣
ዮሐንሶን ተነሳ ከነቤተሰቡ
ለበጋ እረፍታቸው ከገጠር ሊገቡ፣
ለሽርሽር ሄዱ በብስክሌታቸው
ትንሽ ራቅ ብለው ከገጠር ጎጆአቸው፣
ቀላል ምግብ ቀምሰው
ከፀሐዩ ሙቀት ተዘርረው ውለው
ማምሻ ፀሐይ ስትጠልቅ ገቡ ከቤታቸው።

1995

## እቃዣለሁ

የሰው ልጅ መቧጨቅ መባላቱን ትቶ
ለስልጣን ለነዋይ መጋደሉ አብቅቶ
ለመኖር ሲወስን በአንድ ላይ ተስማምቶ፣
በእውኔ እቃዣለሁ!
በሽታና ረሀብ ከምድር ሲጠፉ
ዕውቀትና ልማት በአንጻሩ ሲስፋፉ
ሰዎች በዕድገት ባህር ወደፊት ሲቀዝፉ፣
በእውኔ እቃዣለሁ!
ሰውና ተፈጥሮ እርቅሲ መስርቱ
ጥበቃ ሲያገኙ አእዋፍ አራዊቱ
በቅጡ ሲያዙ የባህር ፍጥረታት የምድር ዕፅዋቱ።
በእውኔ እቃዣለሁ!
ከፆታ ከዕድሜ ከቀለም ልዩነት
ከዕውቀት ከነዋይ ከሌላም ባሻገር
ሁሉም ሊረዳዳ ሲጥር ሲፍጨረጨር፣
በእውኔ እቃዣለሁ!
አዎ! ቅዠት ሕልም ቢሆን
ሕልምም እውነት ቢሆን
ምንኛ ደግ ነበር።

1996

## ትላንት፣ ዛሬ ነገ

ዛሬ ትላንትና ነገ ዛሬ ሆኖ
ዘንድሮ አምና ሆኖ መጭ አመት ዘንድሮ
ይለዋውጠዋል የሰውን ልጅ ኑሮ።
ትላንት የደላው ሰው ዛሬ እየየ ይላል
ትላንት ያለቀሰ ዛሬ ይፍለቀለቃል።
ከበርቴ የነበረ የዕለት ጉርሱን ያጣል
ደሀው ተሳክቶለት ሊከብር ይችላል።
በዛሬው ሕይወትህ ያለቅጥ ደስታ
ያለቅጥ ብስጭት
እንዳይሰጥ ለጉዳት፣
ትላንትና ዛሬን ነገንም ተመልከት
ይሰጡሀልና በቂ የሕይወት ትምህርት።

1996

## ጢስ እሳት

የውሃ ነዶ በውሃ ላይ ወረደ
ከላይ ወደ ታች ተዥጎደጎደ፣
አግድም መጓዙን ትቶ አቆልቁሎ ወረደ
እርጋታውን ተወና ራስ በራሱ ላይ ተናደ።
ያለመጠን ፈጠነ ነጭ አረፋ ደፈቀ
ከትራፊውፈነጠቀ አካባቢውን አጠመቀ፣
በልምላሜ ተከበበ በቀስተ ደመና ተዋበ
እዩኝ ስሙኝ በማለት የሕዝብ አትኩሮትን ሳበ፣
እያቅራራ እያጓራ ጢስ እሳት ጦፈ ነደደ
ግርማ ሞገሱን ተላብሶ ጢስ እባይ ሄደ ነጎደ።

1996

## ባይተዋር

ለሰው ለአገሩ
ለተክሉ ለምድሩ
ለባህል ለአየሩ፣
ለሁሉም ባይተዋር
ለቋንቋው ለቀልዱ
ለባህል ለልምዱ፣
ለምግብ ለመጠጡ
ለአጠቃላይ ለውጡ
ለሁሉም ባይተዋር
ሲኬድ ከሰው አገር።

1996

## ብቸኝነት

በጎዳናው ሁሉ ሰው ይመላለሳል
በየጎረቤቱም ሰው ይኖርበታል
ከሚኖርበት ቤት ተሌቭን ያያል
ሬድዮም ያዳምጣል
ጋዜጣም ያነባል፣
ሰላምታ የሚሰጡት የሚያነጋግሩት
ብዙ ሰዎች አሉት፣
እናትና አባቱን አክስት አጎቶቹን
አብሮ አደጎችና የቅርብ ጓደኞቹን
ባህልና ቋንቋውን
አየሩን ምድሩን፣
ትቶ ስለመጣ ከተወለደበት
ይሰማዋል ዛሬም ፍጹም ብቸኝነት።

1997

## የአገር ቤት አውድ አመት!

የአመት በአል ሽር ጉድ
ላይ መውጣት ታች መውረድ
ቆንጆ ጠላ ጠምቆ
ድፎ ዳቦ ደፍቶ፣
ቄጠማ ጎዝጉዞ
የባህል ልብስ ለብሶ፣
በቅመም ያበደ የዶሮ ወጥ ሰርቶ
የጤፉን እንጀራ በደምብ አሰናድቶ፣
ከአንድ ገበታ ላይ ሁሉም አብሮ ቀርቦ
ሲጎርስ ሲጎራረስ ዙርያ ተሰብስቦ፣
ዘመድ ከዘመዱ ድግስ ሲጠራራ
በየግብዣው ቦታ ጫወታ ሲደራ፣
ሰዎች በየቦታው እንኳን አደረሰህ!
እንኳን አደረሰሽ!
የሚባባሉበት
ትዝ ትዝ ይለኛል የአገር ቤት
አውደ አመት!

1997

ድግስ

ምግብ ተዘጋጀ
መጠጥ ቀረበ
ጎረምሳው ኮረዳው በብዛት ጎረፈ
በናፍቆት ሰላምታ ሰው ተቃቀፈ
ጉንጭ ለጉንጭ ተጋጨ
ለሙዚቃው ምሽት ጎረምሳው አፏጨ።
ለታላቁ ምሽት ዘፋኝ ድምፁን ሰጠ
ሰው ተገባብዞ እስክስታው ቀለጠ።
እንግዳው በሙሉ በሙዚቃው መድረክ ተውረገረገበት
ዳንኪራ መታበት ቨዋልስም ደነሰበት፣
ጠዋት በንጋት ላይ ያች ቆንጆ ጊዜ ስትሟጠጥበት
ካፖርቱን ደረበ ለመጓዝ ወደ ቤት
"ሀንግ ኦቨር" ሊያሳልፍ ጥቂት በመተኛት።

1997

## ጨረቃና ፀሐይ

ሰማዩ ፍም መስሎ በአማረበት ምሽት
ብርሃን ስትሰጠን የዋለችው ፀሐይ
ሙቀት ስትለግሰን የዋለችው ፀሐይ
ጊዜው ስለመሸ ደህና እደሩ ብላ ከኛ ልትለያይ
አለች በጉዞ ላይ፣
ከወጣች ጀምሮ ጠዋት በማለዳ
እያዘጋገመች ረዠም ጊዜ ወስዳ
ከቤትዋ ልትገባ ልትሄድ ለአዳሯ
ከሩቅ ትታያለች ቆማለች ከበሯ፣
በስተፀሐይ መወጫ ጨረቃ ብቅ አለች
የምሽቷ ንግስት ጨለማን ገፋፊ እኔ ነኝ እያለች፣
ጨረቃ ልትደምቅ ፀሐይዋ ልትጠልቅ
በአንድ ምሽት ሰማይ ሲተያዩ ከሩቅ፣
ይመስላሉ ላየ ምንም ቢራራቁ
የተነፋፈቁ
ግን ዕድል ፋንታቸው ያላገናኛቸው
መዳዝ ያለባቸው ወደየፊናቸው።

1998

## አንድ ቀን

ያለቅጥ ቀዝቅዞ ደመና ቢያንዣብብ
በዝናቡ ብዛት ጎርፍ ቢያጥለቀልቅ
አውሎ ንፋስ ነፍሶ ሁሉን ቢነቀንቅ
መሬት ተንቀጥቅጣ ሁሉን ብታሰቅቅ፣
አንድ ቀን ይሰክናል!
አንድ ቀን ይረጋል!
ድቅድቁ ጨለማ ምድርን ቢሞላ
አራዊት ቢያጓራ የሰው ልጅ ሊበላ
ጨረቃ ከዋክብት ጨርሰው ባይወጡም፣
ጊዜ ይወስዳል እንጅ
አንድ ቀን ይጠራል!
አንድ ቀን ይበራል!
አንድ ቀን ይነጋል!

1996

እውነትን አፋልጉኝ!

ወዳጅ ዘመዶቼ
ሌሎች ወገኖቼ፡
የምታውቁኝና የማታውቁኝ ሁሉ
ወጣት ሽማግሌ ወንድ ሴት ሳትሉ
በቋንቋ በሐይማኖት በዘር ሳትለዩ
የቆዳችሁ ቀለም አህጉር ሳይለያችሁ
በእውነት ፍለጋዬ እርዱኝ እባካችሁ።

እውነትን በሐሰት
እምነትን በክህደት
ከመለወጥ አልፈው
እውነትን ረሽነው
ጉድጓድም ቆፍረው
ሊቀብሯት ይሻሉ አፈር አለባብሰው።

ወዳጅ ዘመዶቼ…

እውነተኛን እውነት
በሐሰት ለውጠው
ለእውነት የቆሙትን በዛቻ አስፈራርተው
በአድማ አሸብረው በግፍ አሰቃይተው
የሐሰት መርዛቸውን በሰፊው ረጭተው
በገንዘብ በዘመድ በወገን መከታ
ለማየት ይሻሉ እውነት ስትረታ።

ወዳጅ ዘመዶቼ…

የሥልጣን ፍራቻ
ወይም አምቻ ጋብቻ
አሊያም የጎረሱት ጉርሻ
አይናቸውን ጋርዶት
እንዳያዩ እውነት
ለእውነት የመቆሙን
ቃለ መሐላውን
የሕዝብ አደራውን
በመተው ወደ ጎን
ይዘው ይታያሉ አካፋ ዶማውን
አፈር ለመመለስ ቀብረዋት እውነትን።

ወዳጅ ዘመዶቼ…

እንደ ግሪኩ ሊቅ መብራት አብርታችሁ
በየአደባባዩ በየቢራቢሮው በየጉራንጉሩ
ባታ ሳይቀራችሁ
በየሰው አዕምሮ በየሰው ሕሊና እየዘለቃችሁ
እውነትን አፋልጉኝ እርዱኝ እባካችሁ።

2002

መሰላል!

አያ እንቶኔ የሚሉት አንድ ወዳጃችን
በመሰላል ወጥቶ ከላይ ከጣራችን
ከታች ያለነውን ቁልቁል እየጠራ
ትእዛዝ ይሰጥ ነበር በደምብ እያብራራ፡፡
እምቢ ያልነውንም
ከስር ከኛ ጋራ ያሉት ዘበኞቹን
እንዲደበድቡን ወይንም እንዲያስሩን
ትእዛዝ እየሰጠ
እጅጉን ተዝናና አለቅጥ ናጠጠ
አለቅጥ አበጠ፡፡
ጣራውን አስፍቶ በደምብ አሰርቶ
ጥቂት ጭፍሮቹንም ወደ ላይ አውጥቶ
ሲበሉ ሲጠጡ አብረው ሲጨፍሩ
ከዚያው ከኛ በላይ ብዙ ዘመን ኖሩ፡፡
ታዲያ አንድ ክፉ ቀን አውሎ ንፋስ መጥቶ
ላዩን ስለናገው
መጠለያ አጥተው ስለቸገራቸው
መሰላል ፍለጋ የግድ ሆነባቸው፡፡
መውጣቱ ቢቀልም መውረዱ ከብዶአቸው
ከታች መሰላሉን የሚይዝላቸው ሰው በማጣታቸው
ከዚያ ከጣርያ ላይ አዳልጦ ጣላቸው
ምንም አልተረፉም እንክትክት ብለዋል
ወጥታለች ነፍሳቸው፡፡

አይ! እኔን አያ እንቶኔ!
አይ! አይ ክፉ መሰላል ሲወጡት ይቀላል
ሲወርዱ ይጥላል አይ ክፉ መሰላል!

2002

ድልድይ!

ወንዝ መሻገርያው ሰው ሰራሹ ድልድይ
ሰው የሚያቀራርብ ዘመድ የሚያስተያይ
ክረምትና በጋ የሚሻገሩበት
ነው ያለአንዳች ችግር የሚገናኙበት።
ፍቅር በሌለበት ሰላም ከአገር ጠፍቶ
መኖር በሚሻበት ሕዝብ ተለያይቶ
ድልድይ ድንበር ሆኖ ሰዎች ያለያያል
አያቀራርብም ፍጹም ያራርቃል።
ሰዎች ከሰዎች ጋር ከእንስሳት ከአራዊት
የሚቃረቡበት የሚፋቀሩበት የሚዋደዱበት
ሰዎች ተነሱና ለፍቅር ለሰላም ድልድይ እንስራለት
ሁሉን የሚያሻግር ወደ ወደደበት ወደፈለገበት
ድልድይ እንስራለት!

2002

ባሕር ሆደ ሰፊው!

ትንሹ ትልቁ ግዙፉ ደቂቁ
እየተፋቀሩ እየተቦአጨቁ
እየተጠራሩ እየተፈራሩ
እየተባረሩ እየተናከሩ
አብረው በአንድነት የሚኖሩበት ቤት
ባሕር በሆዱ ውስጥ ስንት ሚስጥር አለ‹ት፡፡
ቆንጆው መልከ ጥፉው
ወፍራሙ ኮሳሳው
ፈጣን ዘገምተኛው
ባለ ብዙ ቀለም ተፈጥሮ ያደለው
የዚህ ሁሉ ፍጥረት መኖርያው ባሕር ነው፡፡
ባሕር ሆደ ሰፊው
ሲያሻውም ያበላል ሲያሻውም ይበላል
ሲያሻው ይደንሳል ሲያሻውም ይቆጣል ወይንም
ይቀጣል
ሲፈልግ ይቀርባል ሲፈልግ ይርቃል
እንዳሻው አዳሪ እኛ የማናዝበት
ባሕር ሆደ ሰፊው ብዙ ሚስጥር አለ‹ት፡፡

2002

ውጥንቅጥ

ግርማዊ ጃንሆይ
ክቡር ራስ ደጅአዝማች
ካድሬው ጓዱ ታጋይ
አቤት የማዕረጉ ብዛት ሲታይ።
ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ
ሰው በየማዕረጉ ሲለካ
የትላንቱ ባለሥልጣን ይሻራል
በባለቀኑ ዘብጥያ ይወርዳል።
አንዱ ላብአደር ሲል ሌላው ወዝአደርን ይመርጣል
አንዱ ሲያሸንፍ ሌላው ያቸንፋል
አንዱ ነጭ ሽብር ነዛህ ተብሎ
በቀይ ሽብር ይደመሰሳል።
አንዱ ጸረ-ዲሞክራሲ ይባልና
ወይም ሙስናን በማስፋፋት ይከሰስና
ከፖሎቲካው መድረክ በቀይ ካርድ ይባረራል።
አቤት የስሙ ብዛት ለሚጠሉት
ለሚጎመጁት ሊበሉት
አናርኪስት ቀኝ መንገደኛ ተገንጣይ
ጠባብ ብሄረተኛ አታላይ
ኦ ኤል ኤፍ ጎጠኛ
ትምክህተኛ ነፍጠኛ
«ሁሉም መጥፋት ያለባቸው
ምህረት የማይሰጣቸው።»

ዳሩ ሁሉም በየፊናው ይኖራል
አንዱ እየሄደ ሌላው ይተካል
ሌላ ወዳጅ ሌላ ጠላት
እናያለን ከአመት አመት::
አንዱ አንዱን ማጣጣሉ
እርስ በርስ መጋደሉ
ውጥንቅጡ
ይቀጥላል ልቦና እስክንገዛ
እስክንረዳ ይህ መንገድ እንደማያዋጣ::

2002

## ትውልዳችን

ተገኘ ገኘን ሳይወድ ተቀብሎ
ጭሰኛው በጉልተኛው ተጎሳቁሎ
ግብር ከፍሎ
ኩዳድ አርሶ እርቦ ሰፍሮ
ከዚያም አልፎ ታስሮ
ሚስቱን ልጁን ሳይወድ አስደፍሮ
ተጥሎ ጀርባውን በጅራፍ ተገርፎ
ከዚህም ሁሉ አልፎ ተርፎ
ፍሬ ዘሩ ተቀጥቅጦ
ነበር ኑሮው በችግር ማጥ ተውጦ።
ታዲያ ትውልዳችን መደብና ዘር ሳይለይ
እምቢ አሻፈረኝ ብሎ ይህን ግፍ ላያይ
ተነስቶ በአንድነት በሕብረት
ታገለ ሸንጡን ገትሮ ሊለውጥ ያንን ሥርዐት።
እሱም እንደነኛ ምስኪኖች
ታሰረ ተሰቃየ አካሉ ጎደለ ተገደለ
በየጎዳናው ላይ ተጣለ።
ታዲያ ያ ያልታደለ ወጣት ትውልድ
ድንበር የለሽ መስዋዕትነት ቢከፍልም
የዚያ ደሃ ሕዝብ መከራ ዛሬም ብዙ አልተለወም።

2002

## ጠዋት በማለዳ!

ጠዋት በማለዳ
በሰላም አውለኝ ብየ እንደተነሳሁ
የአገር ቤት ወፎች
ሲዘምሩ ሰማሁ፡፡
ገበሬው ለእርሻው
በጠዋት ተነስቷል
ማለዳም በጠዋት
ውሃ ልትቀዳ ወደ ወንዝ ወርዳለች
ከዚያም ተመልሳ
እሳት አቀጣጥላ
ቡና ልታፈላ
የቡና ቁርሱንም ቆሎ ልትቆላ
ቤቱን ልታጸዳ
የቀኑን ጉዞዋን እንዲሁ ልትገፋ
አያታለሁ ጠዋት ስትል ቀና ደፋ፡፡
ከበራፍ ስወጣ
ደመናና ጭጋግ የሳሩ ላይ ጤዛ
ሲወጣ የማየው ጢስ
ከየጎጆው አናት
ከሜዳ ያሉትን ከብቶች ስመለከት
ይህን ሁሉ ትርዒት ቆሜ ሳተኩርበት
እርቄ እሄዳለሁ በተመስጦ ብዛት
እነሱ ይኖሩታል ይህን ዕለት ከዕለት
ለእኔ ግን ትርዒት ነው የምመሰጥበት
የምገረምበት የምደሰትበት የምተክዝበት፡፡

2005

የሰላም አጋር ነኝ!

ለሀሳብ ልዩነት ጦሬን የማልሰብቅ
ለአመለካከቴ የማላነሳ ትጥቅ፡
ሰላምን በሰላም ላመጣ የምሻ
በዚህ አቋሜ የጠናሁ እስከ መጨረሻ፡
የሰላም ወታደር የሰላም አርበኛ
የዲሞክራሲ ወገን የፍትህ ጓደኛ፡
በሾለ ብዕሪ በሰላ አንደበቴ አነጣጥሮ ተኳሽ
ነኝ የሰላም ታጋይ የወገን ደም መላሽ።

እያልኩ እጮሃለሁ
ፍቅር መተማመን መከባበር ይስፈን፡
የሰው ሰውነቱ
ቤተሰብ ንብረቱ
አመለካከቱ
ቋንቋው ሀይማኖቱ
ይከበር እላለሁ።

ጾታና ዕድሜ ሳንለይ
ልዩነቶችንም በክፉ ዐይን ሳናይ፡
ልዩነት ለአንድነት መሰረት እንዲጥል
በሰላሙ መንገድ ወደፊት እንቀጥል።

በነጻ የሀሳብ መግለጽ መብቶችን ማፈኑ
የሰላም ሀይሎችን ማስፈራራትና በሀሰት መኮነኑ
ንጹሃን ዜጎችን ማሰር መደብደቡ ደግሞም መረሸኑ፡
ኢ- ዲሞክራሲያዊ ስልቶች ስለሆኑ
ውለው አይደሩ ይቁሙ ከአሁኑ፡፡

ዛቻ ማስፈራራት እስርና ግድያ
የኢ- ፍትህ ስርአት ነውና መለያ፡
የሰላም ይፍትህ ወገኖች በሙሉ
ለሰብአዊ መብቶች በአንድነት ታገሉ፡፡

የዘር የሐይማኖት የጾታ ልዩነት
ሳይገታን በህብረት
አገር እንድትወጣ ከኢ-ፍትህ ስርዐት፡
የሰላም ታጋዮች የፍትሕ አርበኞች ሆነን እንቁምላት
ሰላማዊ እምቢታን እንደግፍ በአንድነት!

2005

አሁን!

ትላንት ትዝታ ነው
የተወለድንበት ያደግንበት ዘመን
በበጎ ድርጊቶች የፈነደቅንበት
በዘመዳችን ሞት በጣም ያዘንበት
ያመነው ሲከዳን የተማረርንበት
ባልጠበቅነው መንገድ በሌሎች ውለታ
ሊሰማን የቻለው መጠንየለሽ ደስታ
ያ ሁሉ ታሪክ ነው ያለፈ ትዝታ፡፡
የመጪው ዘመን ሕልም
የኑሮ መሟላት
የሕይወት መሳካት
ድቅን ወለል ብሎ የሚታይበቱ
ተስፋ እሚጣልበት ሁሉም መሳካቱ
ያ ደግሞ ምኞት ነው
የምንካፈለው እኩል ከሁሉም ሰው፡፡
ትዝታም ጥሩ ነው ይኑር ምን አለበት
ምኞትም መልካም ነው ለወደፊት ሕይወት
ዛሬ ግን ዕንቁ ናት አሁን ያለንባት
ስለዚህ እንኑርባት ተግተን እንስራባት
እንደሰትባት፡፡

2006

ለሁለተኛው ሺ ዓመት ምህረት

የጥላቻ መንፈስ ውጣ
የፍቅር መንፈስ ግባ::

የመናናቅ መንፈስ ውጣ
የመከባበር መንፈስ ግባ::

የመጠራጠር መንፈስ ውጣ
የመተማመን መንፈስ ግባ::

የግትርነት መንፈስ ውጣ
የመመካከር መንፈስ ግባ::

የኢ-ሰብአዊነት መንፈስ ውጣ
የርህራሄ መንፈስ ግባ::

የአድሎ መንፈስ ውጣ
የሐቀኛ ፍትሕ መንፈስ ግባ::

ካለአግባብ የመበላለጥ መንፈስ ውጣ
የእኩልነት መንፈስ ግባ::

የጦርነት መንፈስ ውጣ
የሰላም መንፈስ ግባ::

የመለያየት መንፈስ ውጣ
የአንድነት መንፈስ ግባ።

የጠብ መንፈስ ውጣ
የዕርቅ መንፈስ ግባ።

መጪው መቶና ሺ ዓመት
ኢትዮጵያ ከድህነት የምትላቀቅበት
ኢትዮጵያዊያንና ሌላውም የዓለም ሕዝብ
በሰላም
በፍቅር
በጤናና
በብልጽግና የሚኖሩበት ይሁን!

2007